homes victoria

50 Lonsdale Street,
Melbourne Victoria 3000
GPO Box 4057, Melbourne Victoria 3001
DX 210081

**OFFICIAL**

ነዋሪ
12 የሆላንድ ኮርት እና 120 ሬስኮርስ ሮድ
ፍሌሚንግተን

ውድ ነዋሪ

ስለ ሆምስ ቪክቶሪያ ታልቁ የቤቶች ግንባታ (Big Housing Build) እድገት እና ስለ ሰማይ-ጠቀስ ፎቆች የመልሶ ማልማት መርሃ ግብር ለማሳወቅ እየጻፍንልዎት ነው።

የፕሮግራሙ ቀጣይ ምዕራፍ አሁን በ 7 አዳዲስ ቦታዎች በመካሄድ ላይ ነው። ይህ ማለት አሁን በ9 መንደሮች ወይ ሳበርቦች ለሚኖሩ የአሁኑ እና የወደፊት ነዋሪዎች የተሻሉ፣ ደህንነታቸው የተጠበቀ እና ምቹ የሆኑ ቤቶች ወደ ማቅረቡ እያመራን ነው።

## ዛሬ ይፋ የተደረገው ምንድን ነው?

ዛሬ፣ እነዚህን ሕንፃዎች እንደገና ስለማልማት ከነዋሪዎች ጋር ተነጋግረናል፦

- 25 እና 27 ኪንግ ስትሪት፣ ፕራሃን
- 150 ኢንከርማን ስትሪት፣ ሴይንት ኪልዳ
- 150 ቪክቶሪያ አቬኑ፣ አልበርት ፓርክ
- 159 ሜልሮዝ ስትሪት፣ ኖርዝ ሜልበርን
- 29 ክራውን ስትሪት፣ ፍሌሚንግተን
- 94 ኦርመንድ ስትሪት፣ ኬንሲንግተን

በእነዚህ ሕንፃዎች ውስጥ ከሚኖሩ ነዋሪዎች ጋር በመደበኛነት እየተገናኘን ነው እና **ከጁላይ 2026 እስከ ፌብሩዋሪ 2028 ድረስ** ወደ ተስማሚ ቤት እንዲዛወሩ ለመርዳት ከእነዚህ ቤተሰቦች ጋር በቅርበት እንሰራለን።

## መዛወርዎን በመደገፍ ላይ ነን

በአሁኑ ጊዜ እርስዎን እና ጥቂት ቁጥር ያላቸውን በ12 ሆላንድ ኮርት እና በ120 ሬስኮርስ ሮድ የቀሩትን ቤተሰቦች ዝውውር ለማቀናጀት ድጋፍ እየሰጠን ነው።

**በአሁኑ ጊዜ የተሰጠዎት የመኖሪያ ቤት ለመውሰድ እያሰቡበት ከሆነ፣** በተቻለ ፍጥነት ውሳኔዎን ለማዛወር ቡድን እንዲያሳውቁ እናበረታታዎታለን።

**አዲስ ቤት ከተሰጠዎት፣** የሚዛወሩበት ቀን ውሳኔ ከእኛ ጋር ለማጠናቀቅ ጊዜው አሁን ነው።

## ያስታውሱ

**መብቶችዎ ተመሳሳይ ሆነው ይቀጥላሉ።** በመኖሪያ ቤት ተከራዮች ህግ (Residential Tenancies Act) መሰረት አዲሱ ቤትዎ በመኖሪያ ተመሳሳይ መብቶች እና ጥበቃዎች ይኖረዋል።

**በመዛወርዎ ወቅት የሚደረግ እገዛ።** ዕቃ የሚያዘውሩ እናዘጋጃለን፣ አስፈላጊ ከሆነ በማሸግ እና የታሸገውን በመክፈት እንረዳለን፣ እንደ ስልክ፣ ኢንተርኔት እና የፖስታ ማዘዋወር ያሉ ግንኙነቶችን እናዘጋጃለን እና ለሁሉም ምክንያታዊ የመዛወር ወጪዎች እንከፍላለን። እንዲሁም ማንኛውንም ያልተፈለጉ ዕቃዎችን እንዲያስወግዱ እንረዳዎታለን።

**ተመልሶ መምጣት።** የመልሶ ግንባታው ሲጠናቀቅ በቀጣይ ፍላጎቶችዎ፣ ብቁነትዎ እና የአዳዲስ ቤቶች ተስማሚነት ላይ በመመስረት ወደ ሰፈርዎ መመለስ ይችላሉ።

## በሰፈራችሁ

ማፍረስ ለመጀመር እየተዘጋጀን ሳለ፣ በአዲሶቹ ቤቶች ውስጥ ምን እንዲኖር እንደሚፈልጉ ነዋሪዎች የሰጡትን አስተያየት ግምት ውስጥ እያስገባን ነው። ራዕዩ በጥሩ ሁኔታ በተነደፈ እና በደንብ በተገናኘ ሰፈር ውስጥ ጥራት ያላቸው አዳዲስ ቤቶች መገንባት ነው።

ይህ በእንዲህ እንዳለ፣ በሆላንድ ኮርት ግንባታ ውስጥ ያሉት አዳዲስ ቤቶች እና የማህበረሰብ መገልገያዎች በዚህ አመት ሊጠናቀቁ ነው እና በቅርቡ የአዲሱ 5000 ካሬ ሜትር ማዕከላዊ ፓርክ ንድፎችን እናካፍላችኋለን።

ከሰላምታ ጋር

**Simon Newport**
ዋና ሥራ አስፈፃሚ
ሆምስ ቪክቶሪያ

28/01/2026